የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር

ሀሰተኛ ሰነድ አቅርበው የተገኙ የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች ተጠያቂ ስለሚደረጉበት ሁኔታ የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ

ሰኔ 2010 ዓ.ም

ሀሰተኛ ሰነድ አቅርበው የተገኙ የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች ተጠያቂ ስለሚደረጉበት ሁኔታ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ

መግቢያ

አንዳንድ የመንግስት ሰራተኞች እውቀቱና ልምዱ ሳይኖራቸው የሀሰት ማስረጃ በማቅረብ በመንግስት ተቋማት የመቀጠርም ሆነ በእድገት ከአንዱ ደረጃ ወደሌላው በቀላሉ መሸጋገር የሚችሉበትን ሁኔታ መፈጠሩን የሚጠቁሙ ሁኔታዎች በመኖራቸው ይህንኑ ችግር በወቅቱ ለመቅጨት አንድ ወጥ አሰራር መዘርጋት ተገቢ ይሆናል። በመሆኑም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከሰራተኞች የቀረቡ የትምህርት፣የስራ ልምድ እና ልዩ ልዩ የሙያ መረጃዎች በሁሉም የፌዴራል መስሪያ ቤቶች የማጣራት ስራ እንዲጀመር አስደርጓል። በዚህም በቅድሚያ ሀሰተኛ ሰነድ ማቅረባቸውን ራሳቸው አምነው እንዲያሳውቁ እድል በመሰጠቱ ይህንኑ ተጠቅመው ራሳቸውን ያጋለጡ ሰራተኞች ላይ የሚሰጠው ውሳኔን የሚያመላክት መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል።

በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ አንቀጽ 375 እና 378 እንዲሁም በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 1 ሀሰተኛ ሰነድ ማቅረብ በወንጀል እንደሚያስቀጣ የተደነገገ ቢሆንም በፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) እና (ሠ)ላይ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የወንጀል የማቋረጥ ወይም ክስ የማንሳት ስልጣን ለፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ተሰጥቷል። በዚሁም መሰረት አሁን ካለው የችግሩ አሳሳቢነት አንፃር አጠቃላይ መርሁ የተጠቀሰው ቢሆንም ጉዳዩን በልዩ ሁኔታ በማስተናገድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍታት የተዘጋጀው ይህ መመሪያ ለፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ቀርቦ ተቀባይነት በማግኘቱ ተግባራዊ እንዲደረግ ተወስኗል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ፤

ይህ መመሪያ " ሀሰተኛ ሰነድ አቅርበው የተገኙ የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች ተጠያቂ ስለሚደረጉበት ሁኔታ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ፤

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. "አዋጅ" ማለት የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ነው::
2. "ሀሰተኛ ማስረጃ" ማለት የመንግስት ሰራተኛው በቅጥር ወይም ከቅጥር በኋላ ያቀረበው የትምህርት፣ የስራ ልምድ ፣ የብቃት ማረጋጋጫ ሰርተፍኬት ፣ የሙያ ማስረጃ እና የስራ መልቀቂያ ማለት ነው::
3. "ሚኒስቴር" ማለት የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ማለት ነው::

3. የጸታ አገላለጽ፤

በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ላይ በወንድ ጸታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል::

4. አላማ

በፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በማገልገል ላይ የሚገኙ የመንግስት ሠራተኞች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ትክክለኛነትን በማጣራት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ነው::

ክፍል ሁለት

5. የማጣራት ስራው አመራርና አደረጃጀት

ሀ) ሀሰተኛ ማስረጃዎች የማጣራቱ ስራ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚመራ ይሆናል::

ለ) ማንኛውም የፌዴራል መንግስት መስረያ ቤት የማስረጃ ማጣራት ስራውን የሚያስፈጽም ኮሚቴ ማቋቋም አለበት::

ሐ) የማስረጃ አጣሪ ኮሚቴው የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ያቀረቧቸውን የትምህርት፣ የስራ ልምድና የሙያ ማስረጃዎች ትክክለኛነት መረጃዎቹን ከሰጡ ተቋማት በማቅረብ ያረጋግጣል፡፡

መ) የማስረጃ አጣሪ ኮሚቴው በየወሩ መጨረሻ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስራው የደረሰበትን ደረጃ የሚያሳይ ሪፖርት ይልካል፡፡

6. በፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚቋቋሙ ኮሚቴዎች አደረጃጀት

ሀ) በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም ..... ሰብሳቢ

ለ) የመ/ቤቱ የስነ ምግባር ኃላፊ/መኮንን..... አባል

ሐ) የመ/ቤቱ የሪፎርምና መልካም አስተዳደር ዳይሬክተር.....አባል

መ) የመ/ቤቱ የህግ ጉዳዮች ዳይሬክተር.....አባል

ሰ) የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክተር..... አባልና ጸሃፊ ናቸው፡፡

7. በአንቀጽ ስድስት ከተዘረዘሩት ውስጥ ሀላፊ ያልተመደበባቸው የስራ ክፍሎች ካሉ በጎደሉት ምትክ የመስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ ሌላ ሰው መርጠ እንዲመደብ ያደርጋል፡፡

8. የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሀላፊነት

ሀ) በፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚካሄደውን ማስረጃዎችን የማጣራት ሂደት በበላይነት ይመራል፡፡

ለ) በፌዴራል የመንግስት ተቋማት ከተቋቋሙ የመረጃ አጣሪ ኮሚቴዎች ለሚቀርቡ ሪፖርት እየመረመረ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡

ሐ) ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለተቋቋሙ ኮሚቴዎች ለሚቀርቡ የምክርና የድጋፍ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

መ) በፌዴራል የመንግስት አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚካሄደውን መረጃ የማጣራት ሂደት የሚመለከት የድርጊት መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ እንደ አስፈላጊነቱ መርሀ ግብሩ እንዲከለስ ያደርጋል፡፡

ሰ) በፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ መ/ቤቶች ለተቋቋሙ ኮሚቴዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣

ረ) ሀሰተኛ ማስረጃ እንዳያያዙ የተለዩትን፣ ያገኙት ጥቅም የተሰረዘባቸውን፣ በዲሲፕሊን ወይም በህግ እንዲቀጡ የተሰወነባቸውን ሰራተኞች በሚመለከትና በፌዴራል ደረጃ የመረጃ ማጣራት ስራው ያለበትን ደረጃ በሚመለከት ለመንግስት በየ 3 ወሩ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

9. የፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሀላፊነት

ሀ) ከሚኒስቴሩ የተላለፈውን የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት ያደረገ የተቋም ዝርዝር እቅድ ያዘጋጃል፣

ለ) የማጣራት ሂደቱ አፈጻጸም ላይ ለመ/ቤቱ ሰራተኞች ገለጻ ያደርጋል፣ ሰራተኛው በማጣራቱ ሂደት ላይ ተሳትፎ እንዲኖረው ያበረታታል፡፡

ሐ) በወጣው እቅድ መሰረት የመ/ቤቱን ሰራተኞች የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃዎች ትክክለኛነት ያጣራል፣ ሀሰተኛ ሆነው የተገኙ ማስረጃዎችን ለይቶ እንዲሁም የተወሰደውን እርምጃ በሚመለከት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

መ) በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ መሰረት ወቅቱን ጠብቆ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል፣

ክፍል ሶስት

የተጠያቂነት ሁኔታና እርምጃ አወሳሰድ

10. የሀሰተኛ ማስረጃ ማቅረባቸውን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አምነው ያጋለጡ የመንግስት ሰራተኞችን በተመለከተ

ሀ) ሠራተኞች የተሰጣቸውን ሀሰተኛ ማስረጃ ያያዙ መሆኑን የእምነት ቃላቸውን በጽሁፍ ለተቋሙ ኮሚቴ በተሰጠው የጊዜ ገደብ እንዲያቀርቡ እድል እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

ለ) ሀሰተኛ ማስረጃ ከፋይላቸው አያይዘው ጥቅም ያገኙና የይቅርታ ማመልከቻቸውን መስሪያ ቤቱ በሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በመስሪያ ቤቱ ለተቋቋመው ኮሚቴ በማንባር ካቀረቡ ያገኙት ጥቅም እንዲሰረዝና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው በማድረግ ከተጨማሪ ቅጣት ነጻ ይሆናሉ፡፡

11. ሀሰተኛ ማስረጃ ስለማያያዛቸው በቀረበ ጥቆማ መነሻነትም ሆነ መስሪያ ቤቱ ባደረገው አጠቃላይ የመረጃ ማጣራት የተረጋገጠባቸው ሰራተኞችን በተመለከተ፣

ሀ) የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 93 በተደነገገው መሰረት ሀሰተኛ ማስረጃ ማቅረቡ የተረጋገጠበት የመንግስት ሰራተኛ በአስተዳደራዊም ሆነ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚደረግ የተገለጸው ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

ለ) የመንግስት ሰራተኛው ያቀረበው ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ በተ.ቁ 11/ሀ የተጠቀሰውን ሳይጠብቅ በማስረጃው ያገኘው ጥቅም በቅድሚያ እንዲሰረዝ መደረግ አለበት፡፡

12.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 1 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በተከናወኑ የሀሰተኛ ሰነድ ማጣራት በተገኙ የምርመራ ግኝቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ታገሰ ጫፎ

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር

ሚኒስትር